# የአካባቢ ፖሊሲ

*ቀን ፡ ግንቦት 01 ፥ 2016*

---

Allied Gold Corporation ("Allied" ወይም "ኩባንያው") በኃላፊነት ለመሥራት ቁርጠኛ ሲሆን የአካባቢ ጥበቃ እና ኃላፊነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር የዚህ ቁርጠኝነት አስፈላጊ ገጽታ መሆኑን ይገነዘባል።

በዚህ ፖሊሲ አማካኝነት ኩባንያው የሚከተሉትን ለማድረግ ቁርጠኛ ነው፡-

- የአካባቢ ጥበቃ ዕሳቤዎች በሁሉም የኩባንያው ገጽታዎች ውስጥ መካተታቸውን የሚያረጋግጥ የኩባንያ ባህልን ለማስተዋወቅ።
- ተጠያቂ የምንሆንባቸውን የሚመለከቱንን ህጎች እና ሌሎች ተዛማጅ ግዴታዎችን ለማክበር።
- በኩባንያው አፈጻጸም ውስጥ ቀጣይነት ያለው መሻሻልን ለመደገፍ የአካባቢ አስተዳደር ስርዓትን ለማዘጋጀት እና ለማስቀጠል።
- የዘላቂነት ግቦችን ለማሳካት እና የቢዝነስ እንቅስቃሴዎቻችን በአካባቢ ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ አመራርን እና ተጠያቂነትን ለማሳደግ።
- ከአካባቢ ጋር የተገናኙ ዓላማዎችን እና ዒላማዎችን ለማዘጋጀትና እና በመደበኛነት ለመገምገም።
- ከአካባቢ ረገድ አደጋዎችን እና እድሎችን በንቃት በመለየት እና በመገምገም እነዚህን ሀሳቦች በሁሉም የቢዝነስ እቅድ ሂደት ውስጥ በአሰሳ፣ በልማት፣ በኦፕሬሽኖች እና ማዕድን ማውጫን በመዝጋት ሂደቶች ውስጥ ለማዋሃድ ወይም ለማካተት።
- ጉዳቶችን ለማስወገድ፣ ለመቀነስ እና ከተቻለ ለደረሱ ጉዳቶች ካሳ ለመክፈል የአደጋ ቅነሳ/ልዘባ ተዋረድ መዋቅርን ለመተግበር።
- የአካባቢ ተኮር ዓላማዎቻችን ለማሳካት በቂ ሀብቶችን ለማቅረብ።
- የኩባንያ እና የሳይት ደረጃ አካባቢያዊ አፈጻጸምን በመደበኛነት ለመገምገም።
- ሁሉም ሠራተኞች እና ተቋራጮች የየራሳቸውን ኃላፊነት እንዲገነዘቡ ለማድረግ እና ቀጣይነት ባለው ትምህርት እና ሥልጠና እውቀታቸውን የሚያሳድጉባቸውን ዕድሎችን ለመስጠት።
- በሠራተኞች ውስጥ የአካባቢ ግንዛቤን ለማስረጽ።
- በኩባንያው እንቅስቃሴዎች ላይ አስተያየት ለመጠየቅ እና ለማካተት ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀጣይነት ያለው ውይይትን ማዳበር።

***ብዝኀ ህይወት***

- የዓለም አቀፍ ቅርስ በሆኑ ቦታዎች የማእድን ፍለጋን ወይም ማዕድን ማውጣትን መከልከል እና አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ቦታ በህጋዊ መንገድ በተፈቀዱ ወይም በተለዩ ቦታዎች ላይ ሥራን ለማካሄድ።
- የዱር እንስሳት ወሳኝ መኖሪያ ቦታ መጥፋት ምንም እንዳይኖር ጥረት ለማድረግ።

- የባለድርሻ አካላት መብቶችን እና የብዝኀ ህይወት እሴቶችን ለማክበር።

***የኀይል (የኢነርጂ) እና የአየር ንብረት ለውጥ***

- የኀይል ፍጆታን እና የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀቶችን መከታተል እና ይፋ ለማድረግ።
- በአሠራራችን ቁጥጥር ውስጥ ካሉ እንቅስቃሴዎች ጋር የተያያዙ የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀቶችን ለመቀነስ።
- የኃይል ቆጣቢነትን ለማሻሻል ተነሳሽነቶችን/ውጥኖችን ለመተግበር።
- በእኛ የቢዝነሳችን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ የታዳሽ ኃይል አማራጮችን ለመፈተሽ።

***የውሃ ሀብቶች***

- የውሃ ሀብቶችን ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ።
- የንፁህ ውሃ መጠቀምን ለመቀነስ ተነሳሽነቶችን ለመተግበር።
- የውሃ ሀብቶችን ብክለት ለመከላከል መቆጣጠሪያዎችን ለመተግበር።

***አደገኛ ንጥረ ነገሮች***

- አደገኛ ንጥረ ነገሮችን በአስተማማኝ እና ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ ማጓጓዝን፣ መጠቀምን፣ ማከማቸትን፣ አያያዝን እና አወጋገድን ለማስተዳድር።

***በማእድን ቁፋሮ ሂደቱ ውስጥ የተረፈ ምርት እና ቆሻሻ አያያዝ***

- በዋና የኢንዱስትሪ ደረጃዎች ወይም ስታንዳርዶች መሰረት የተረፈ ምርት ማከማቻ በታዎችን ለመንደፍ፣ ለመገንባት፣ ለመስራት እና ለማደስ።

***የቆሻሻ አያያዝ***

- ቆሻሻ ማመንጨትን ለመቀነስ እና የቆሻሻዎቻችንን አያያዝ፣ አቀማመጥ፣ መልሶ አጠቃቀም፣ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋልን ወይም አወጋገድን በአስተማማኝ እና ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ ለማስተዳደር።

***የማዕድን ቁፋሮ ቦታን መልሶ ማልማት እና መዘጋት***

- በማዕድን ቁፋሮው ዘመን በሙሉ በአግባቡ የተገኘ የመልሶ ማልማት እና የመዝጋት ስልቶችን ለማዘጋጀት እና ለመተግበር። እነዚህን ስልቶች በማዘጋጀት የአስተናጋጆቻችን ማህበረሰቦችን እና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ለማሳተፍ።

ይህ ፖሊሲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በAllied ቁጥጥር ስር ለሆነ ቢሮ ወይም ጣቢያ የሚሠሩ ሁሉም ሠራተኞች እንዲሁም በኩባንያው ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር ያሉ ኮንትራክተሮች ይመለከታቸዋል።

ፒተር ማርሮን (Peter Marrone)
**ሊቀመንበር እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ**

ዳንኤል ሬሲን (Daniel Racine)
**ፕሬዚዳንት እና ዳይሬክተር**